፭. "የቆዳ ውጤቶች" ማለት ከቆዳ፣ ከሸራ፣ ከፕላስቲክ ወይም ከሰው ሰራሽ ቆዳ የሚሰሩ ጫማዎች፣ ቦርሳዎች፣ ቀበቶዎችና ጓንቶች፣ ወይም ከቆዳ የሚሰሩ ልብሶች እና የመሳሰሉት ናቸው፤

፮. "የቆዳ ኢንዱስትሪ" ማለት ጥሬ ቆዳ እና ሌጦ ወደ አለቀለት ምርት የመቀየር ሥራንና የቆዳ ውጤቶችን የማምረት ሥራን የሚያጠቃልል ነው፤

፯. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

፫. **መቋቋም**

፩. የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

፭. **የኢንስቲትዩቱ ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት ይሆናል።

፮. **የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

፩. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃግብሮችን ማዘጋጀት፤ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤

፪. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤

፫. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤ ወደዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት ማድረግ፤ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት፤

5. "leather products" means shoes, bags, belts and gloves made from leather, canvass, plastics or artificial leather, or apparels made from leather and the like;

6. "leather industry" means a manufacturing activity inclusive of converting rawhide and raw skin into a final product and manufacturing leather products;

7. any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. ***Establishment***

1. The Leather Industry Development Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2. The Institute shall be accountable to the Ministry.

4. ***Head Office***

The Institute shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. ***Objectives of the Institute***

The objectives of the following Institute shall be to facilitate the development and transfer of leather and leather products industries technologies, and to enable the industries become competitive and beget rapid development.

6. ***Powers and Duties of the Institute***

The Institute shall have the following powers and duties to:

1. formulate policies, strategies and programes that assist in the facilitation of the development of leather and leather products industries; and implement the same upon approval;

2. collect, analyze, organize and transfer to the sector's data center and disseminate to users, as may be appropriate, data necessary for the development of leather and leather products industries;

3. prepare and disseminate project profiles that may be helpful in expanding investments in the leather and leather products industries; conduct feasibility studies for those investors desiring to engage in the sector; follow up project implementation and provide remedies concerning problems encountered during implementation;

፬. በቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤

፭. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ልማት የሚያግዙና ዘርፉን ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፤ ለሠልጣኞችም የምስክር ወረቀት መስጠት፤

፮. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤

፯. በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

፰. ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤

፱. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፤

፲. ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤

፲፩. የግብዓትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፤

፲፪. ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶችን ማከናወን፤

፲፫. ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና የምርት ልማት ሥራ ማከናወን፤

፲፬. ከዩኒቨርስቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ያግዛል፤

፲፭. ለተጠቃሚዎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል መስጠት፤

፲፮. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአግባቡ ክፍያ መጠየቅ፤

፲፯. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

፲፰. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን፡፡

4. advise investors desiring to engage in the leather and leather products industries sector on the selection of technology, negotiation, construction, erection and commissioning;

5. prepare and conduct practical trainings on technology, technical matters, marketing and management and other tailor made trainings, that assist the development and competitiveness of the leather and leather products industries sector; and issue certificates to trainees;

6. conduct studies and researches to promote the development of the leather and leather products industries;

7. provide support and consultancy services concerning production process, production planning and quality control;

8. cooperate with government and private institutions with similar objectives, locally and abroad; and encourage similar co-operations between private institutions;

9. undertake benchmarking studies that facilitate the development and competitiveness of the leather and leather products industries and assist those conducting similar activity in the sector;

10. deliver product-testing services to leather and leather products industries;

11. extend support in the creation of input and output linkage;

12. conduct market study for leather and leather products industries products;

13. identify technologies that can be developed and undertake product development activities;

14. cooperate with universities on product development and human resource development, conduct joint research and assist in the strengthening of local research capacity in the sector;

15. deliver its services to users at one stop shop;

16. collect, as may be appropriate, fees for services it renders;

17. own property, enter into contracts and sue and be sued in its own name;

18. perform such other activities as are conducive to the attainment of its objectives.

## ፯. የኢንስቲትዩቱ አቋም

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩. አማካሪ ምክር ቤት፣

፪. በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፫. አስፈላጊ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

## ፰. የአማካሪ ምክር ቤቱ አባላት

፩. የአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ፡፡

፪. የአማካሪ ምክርቤቱ አባላት ቁጥር እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

## ፱. የአማካሪ ምክር ቤቱ ተግባራት

አማካሪ ምክር ቤቱ፡-

፩. ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፣

፪. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችን ጥናቶችንና ምርምሮችን ይገመግማል፣ አስተያየቱንም ይሰጣል፣

፫. የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፣

፬. የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ አፈፃፀም በየሦስት ወሩ እየገመገመ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ፲. የአማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባዎች

፩. አማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባዎቹን በየሦስት ወሩ ያደርጋል፣ እንዲሁም በመሀሉ በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪. ከምክርቤቱ አባላት መካከል አብዛኛው በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

## 7. *Organization of the Institute*

The Institute shall have:

1. an Advisory Council;
2. a Director General to be appointed by the government; and
3. the necessary staff.

## 8. *Members of the Advisory Council*

1. The Chairperson and members of the Advisory Council shall be drawn from the appropriate government offices and the private sector and appointed by the government.
2. The number of members of the Advisory Council shall be determined as required.

## 9. *Duties of the Advisory Council*

The Advisory Council shall:

1. advice the Institute on its activities;
2. evaluate, and forward its recommendation on, policies, strategies, plans, studies and researches formulated with the view to facilitate the development of the leather and leather products industries;
3. forward its opinions on capacity building programmes;
4. evaluate the implementation of the plans of the Institute every three months and submit reports to the Ministry.

## 10. *Meetings of the Advisory Council*

1. The Advisory Council shall meet every three months, and may hold meetings in the mean time on matters of urgency.
2. There shall be a quorum where the majority of the members of the Council are present at a meeting.

## 11. *Powers and Duties of the Director General*

1. The Director General shall be the chief executive officer of the institute and shall, direct and administer the activities of the Institute.
2. Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:
   a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;
   b) employ and administer personnel of the Institute in accordance with directives to be approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስ ቴሩ ያቀርባል።

፫. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## ፲፪. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

## ፲፫. የሂሣብ መዛግብት

፩. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰ ይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ፲፬. የተሻረ ሕግ

የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፩/፲፱፻፺፩ (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል።

## ፲፭. መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፩/፲፱፻፺፩ ተቋቁሞ የነበረው የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፭/፲፱፻፺፰ ተቋቁሞ የነበረው የጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል መብትና ግዴታዎች፣ የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ዘርፍን አስመልክቶ ከነበሩት መብትና ግዴታዎች በስተቀር፣ በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

## ፲፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**



c) prepare and submit to the Ministry the strategic plan, annual plan, work programme and budget of the Institute and implement the same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work programme of the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3. The Director General may delegate part of his powers and duties to the employees of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

## 12. *Budget of the Institute*

The Budget of the institute shall be allocated by the government.

## 13. *Books of Accounts*

1. The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.
2. The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or an Auditor assigned by him.

## 14. *Repeal*

The Leather and Leather Products Technology Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 41/1998 (as amended) is hereby repealed.

## 15. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of the Leather and Leather Products Technology Institute established by the Council of Ministers Regulation No. 41/1998 as well as the rights and obligations of the Textile and Leather Industry Development Center established by the Council of Ministers Regulation No. 125/2006, other than those relating to the textile and apparel sector, are hereby transferred to the Institute.

## 16. *Effective Date*

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 7th day of June, 2010.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**